# ሁሉ አዲስ ሲሆን

በተውሶ ማህጸን
በተውሶ ስጋ
በብድር አንቀለባ
በተውሶ አልጋ

በብዙ መቃተት
በስደት ቀን ለሊት

በክረምት በበጋ
በብዙ ፈተና መሽቶ እስከሚነጋ

በክህደት በውሸት
በረሃብ በጥማት

በሃሰት ምስክር
በድብቅ በስውር

በግልጽ ባደባባይ
በምድር በሰማይ

በበትር በጅራፍ በጀርባ ግርፋት
በውርደት በሃፍረት

እንደ እባብ በዛፍ ላይ
በጠራራ ጸሃይ

አራቁት ተሰጥቶ
አንደበት ተዘግቶ

ጩከትን ታግሶ
ውርደትንም ለብሶ

ተንቆ ተጠልቶ
በደዌ ተመትቶ

ህመምን በሙሉ
ለበሶ በአካሉ

በላብ ተለውሶ
በራሱ ደም ርሶ

በሙታን ተከብቦ በቀኝ በግራ
በዚያ በጠራራ

በብድር መቃበር በተውሶ መሬት
ለሶስት ቀን ሙሉ ለሶስት ቀን ለሊት

በምድር የተጣለው
የተወረወረው
ላፈር የተሰጠው

ወራቱን ጠብቆ
በዘመኑ ጸድቆ

ዘሩ በቀለና
ምድርን ፈንቅሎ በርግዶ ወጣና

ሞትን እንድ ትቢያ በትኖ ጣለና
አራገፈውና
ህይወት አወጀና

እንደ ሊባኖስ ዛፍ በቁመት በስፋት
አብዞቶ አደገና ጥላ ለደከሙት
ማረፊያ ለዛሉት

በብድር ግንዛት
በተውሶ ጉድጓድ ግብአተ መሬት

አንድ ሆኖ ሞቶ
አንድ ሆኖ ተቀብሮ በመቃብር ገበቶ

እኔን አንተን ይዞ እልፍ ሆኖ ተነሳ
የናዝሬቱ የሱስ የይሁዳ አንበሳ

በተውሶ ስጋ የተውሶን ሃጢያት
በተውሶ ዛፍ ላይ የተውሶን ህይወት

የብድርን በደል አራግፎ ከላዩ
አሸንፎ ጥሎት ቆሞ ከበላዩ

በአዲሱ ህይወት በከበረው ስጋ
የሞትም ጨለማ በድንገት ሲነጋ

እስራት ሲፈታ ቀንበር ሲንከታከት
ጨለማ ሲበራ ደምቆ እንደ ከዋክብት

የተውሶው ገላ ከነጣጣው ወድቆ
የተሰዋውም በግ በትንሳኤ ደምቆ

ቀኑ እንዳልጨለመ መስቀሉ ሸፍኖት
የፍጥረታት ጣጣ መከራ ተጭኖት

በለሊት ውጋገን ጨለማው ሲበራ
በትንሳኤው ብርሃን በትንሳኤው ጮራ

መጨረሻው ጠላት ሞት በሞት ተሽሮአል
ትንሳኤው ታውጆ ትንሳኤው ተነግራል

ሲኦል ማሸነፊያህ ድል መምቻህ ተመትቷል
ስልጣንህ ተሽሮ ህግህ ተሰርዛል

እንግዲህ በሃጢያት
በሞትም ባርነት

እስረህ አትገዛም ትሳኤው ታውጇል
ለኔም ላንተም ላንቺም ፋሲካችን ታርዷል

ዘውዱ ሳህሉ
3/20/2008

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot****. You may contact Zewdu Sahlu  for comments at*** *zewdu_michael@yahoo.com*